የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፯
አዲስ አበባ ታህሳስ ፫ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24rd Year No.7
ADDIS ABABA 12th Decemeber, 2017

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፯/፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በኬኒያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በሞያሌ ድንበር ጣቢያ የጋራ ቁጥጥር፣ሥነ ሥርዓት፣ አገልግሎቶችና አስተዳደር በተመለከተ የተደረገውን የሁለትዮሽ ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ……………………………………………ገጽ ፱ሺ፮፻፷፬

## Content

**Proclamation No.1057/2017**

**Bilateral Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of Republic of Kenya on joint boarder controls, procedures, facilities and management at Moyale Border Post Ratification Proclamation …………………………………………Page 9664**

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፯/፪ሺ፲

**<u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በኬኒያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በሞያሌ ድንበር ጣቢያ የጋራ ቁጥጥር፣ሥነ ሥርዓት፣ አገልግሎቶችና አስተዳደር በተመለከተ የተደረገውን የሁለትዮሽ ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሰት እና በኬኒያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ሚያዝያ ፲፭ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም. በሞያሌ ድንበር ጣቢያ የጋራ ቁጥጥር፣ሥነ ሥርዓት፣ አገልግሎቶችና አስተዳደር በተመለከተ የተደረገውን የሁለትዮሽ ስምምነት አዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም ባደረገው መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩)እና(፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### PROCLAMATION NO. 1057/2017

**<u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE BILATERAL AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF REPUBLIC OF KENYA ON JOINT BOARDER CONTROLS, PROCEDURES, FACILITIES, AND MANAGEMENT AT MOYALE BORDER POST.</u>**

**WHEREAS**, the bilateral Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of Republic of Kenya on joint boarder controls, procedures, facilities and management at Moyale Border Post was signed in Addis Ababa on 23rd April 2014;

**WHEREAS** , the House of People Reperesentatives' of the Federal Democratic Republc of Ethiopia has ratified the said bilateral agreement at its session held on the 2nd day of October 2017;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በኬኒያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በሞያሌ ድንበር ጣቢያ የጋራ ቁጥጥር፣ሥነ ሥርዓት፣ አገልግሎቶችና አስተዳደር በተመለከተ የተደረገውን የሁለትዮሽ ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፯/፪ሺ፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>**

፩.በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በኬኒያ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በአዲስ አበባ ሚያዝያ ፲፭ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም በሞያሌ ድንበር ጣቢያ የጋራ ቁጥጥር፣ሥነ ሥርዓት፣ አገልግሎቶችና አስተዳደር በተመለከተ የተደረገውን የሁለትዮሽ ስምምነት በዚህ አዋጅ ጸድቋል፡፡

፪.ስምምነቱ ላይ የሚደረግ መሰረታዊ ማሻሻያ ወደ ስራ የሚገባው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲፀድቅ እንደሆነ መግለጫ ቀርቧል፡፡

**፫. <u>አስፈጻሚ አካል</u>**

ይህን ስምምነት እንዲያስፈጽም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትራንስፖርት ሚኒስቴር በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቷል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፫ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**
**ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as "The Bilateral Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Kenya on joint boarder controls, procedures, facilities and management at Moyale Border Post Ratification Proclamation No.1057/2010".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

1/The bilateral Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of Republic of the Kenya on joint boarder controls, procedures, facilities and management at Moyale Border Post signed in Addis Ababa on 23rd April, 2014 is hereby ratified.

2/ Any substantive amendement made in the agreement shall be ratified by the House of people's Representatives of Federal Democratic Republic of Ethiopia.

**3 .<u>Implementing organ</u>**

The Ministry of Transport Federal Democratic Republic of Ethiopia is hereby empowered to implement this Agreement.

**4 .<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazetta.

**Done at Addis Ababa on this 12th day of December, 2017.**

**MULATU THESOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF THE ETHIOPIA**